# ለኔ ብለህ



ለኔ ብለህ
ኦ አምላኬ ፣
ክቡር ገናና የሆንክ ፣
ኦ ጌታ ፣
የማትለወጥ የማትረታ ፣
ሁሉ ሲቻልህ ፣
ፍጥረት ኣሜን ብሎ ሲገዛልህ ፣
ለኔ ብለህ ፣
እኔን ወደህ ፣
ከአርያም ከዙፋንህ ፣
እኔን ብለህ ወርደህ ፣
ከድንግል ተወልደህ ፣
ሥጋን ለብሰክ ፣
በጥቂቱ ልክ እንደሰው አድገክ ፣
ለመክፈል ዕዳዬን ፣
ለማበስ እንባዬን ፣
እኔን ከፍ ኣድርገክ ፣
አንተ ዝቅ ያልክ ፣
ፍቅር የሆንክ ፣
ኦ ክርስቶስ ፣
አንተ ቅዱስ ፣
ማንነትህን ሳይረዳ ፣
በድያብሎስ እየተነዳ ፣
ስም ሲያወጣልህ ፣
ሰው ሲጠላህ ፣
ፍቅር የሆንክ ፣
ሰው ሲርቅህ እየቀረብክ ፣
ሰው ሲረሳህ እያስታወስክ ፣
ሰው ሲንቅሕ እያከበርክ ፣
ሕይወት የሆንክ ፣
ኦ ክርስቶስ ፣
አንተ ንጉሥ ፣
ለማልረባው ለኔ ብለህ ፣
ዋጋ ከፍለህ ፣
በሕማምህ ፈውሰኸኝ ፣
ሕይወት ሆንከኝ።
ያንተን ሕማም ፣
ያንን ስቃይ ያንን ድካም ፣
ያንን መናቅ ፣
የሊቀ ካህናቱ ሳቅ ስላቅ ፣
የወታደሮቹ ንቀት ፣
የይሁዳ ክደት ፣
ሳስበው ይገርመኛል ፣
ኦ ክርስቶስ ፣
ፍቅርህ እኮ ሁሌም ይደንቀኛል።
ለዓለሙ ዕረፍት የሆንክ ፣
ማረፊያ ኣጥተህ ተንከራተትክ ፣
ከሲያል ሰውን ለማውጣት ፣
ለአዳም የተዘረጋ እጅ ፣
ታሰረ በሰንሰለት።
የአምስት ገበያ ያህል ሕዝብ ፣
የሚያስተውልበት አጥቶ ልብ ፣
በእጅህ እንዳልበላ እንዳልጠጣ ፣
ወታደር ኣጅቦ ሊይዝህ ሲመጣ ፣
መልስህ ፍቅር ነበር ፣
ሰው ቢቆፍርም ያንተን መቃብር ፣
ኦ............... ጌታዬ
ሁሉን እየቻልክ ፣
በትዕግሥት እያሳለፍክ ፣
ግማሹ ምራቁን ሲተፋ ፣
ጉልበታሙ ሲገፋ ፣
ሲገርፍህ ሲያዳፋህ ፣
ንጉሱ ከሆንክ ማነው የሚመታህ ፣
እያሉ እየቀለዱብህ ሲወራረዱብህ ፣
ፍቅር ነበር መልስህ።

ዮሐንስ ዘርፉ
ሚያዚያ 2003
ቤልጀም